# የስኮትላንድ የስደተኞች ጉባኤ
# ገንዘብዎን በስኮትላንድ እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ ይወቁ

scottish refugee council

OISC

የፋይናንሺያል/ገንዘብ አስተምሮት ፕሮጀክት

ኤፕሪል 2011

FLP - Amharic

## የእኛ የገንዘብ/ፋይናንሺያል አስተምሮት ፕሮጀክት

HAPPY TO TRANSLATE

እኛ የምንሰጣቸው የነፃ መረጃ፣ አውደጥናቶች እና ኮርሶች ገንዘብዎን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ፣ እንዲያቅዱ እና ለወደፊት ዝግጅት እንዲያደርጉ እና ከፍጆታዎች ወይም ለማናቸውም ለሚገጥምዎ ሌሎች የገንዘብ ጉዳዮች መፍትሄ እንዲያፈላልጉ ይረዳዎታል። ይህ በራሪ ወረቀት የሚሸፍናቸው ርዕሰ ጉዳዮች በአውደጥናቶቻችን የተሸፈኑ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ማን መሳተፍ እንዳለበት እና አንድ ቦታ ላይ እንዴት ቀጠሮ መያዝ እንደሚቻል የሚገልጽ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ስለ እያንዳንዱአውደጥናቶችጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን የሚሰጥ እና ተጨማሪ የፋይናንሺያል/ገንዘብ ምክርን በጠቅላላው መረጃን ይሰጣል።

### ወርክሾፖቹ በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው?

የአኛአውደጥናቶችየሚያቀርቡት ወይም የሚሰጡት መረጃ ስለ

- ባንኪንግ እና የቁጠባ ሂሣብ
- ስለ በጀት አበጃጀት
- ስለ ገንዘብ አበዳደር
- ስለ ፍጆታ ክፍየዎች
- ስለ ኢንሹራንስ
- ወደ ስራ የመግባት እና
- የራስዎን የንግድ ሥራ እንዴት መጀመር እንዳለበዎ ነው።

### በአውደጥናቶቹ ላይ ተሳታፊዎች እንማን ናቸው?

ማንኛውም ግለሰብ በአውደጥናቶቻችን ላይ ለመካፈል የሚችል ቢሆንም አውደጥናቶች በይበልጥ የሚመለከታቸው የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ደረጃ ላይ ላሉት ግለሰቦች ወይም አገራቸውን የለቀቁት በእንግሊዝ ንጉሳዊ መንግስት ወይም በእንግሊዝ አገር ለመኖር የለቀቁትን ግለሰቦች ነው። አውደጥናቶቹ በአመቱ በሙሉ በመደበኛነት በግላስጎው ለባሉበት አካባቢዎች በሙሉ የሚካሄድ ነው። የጉዞ ወጪዎች የሚከፈሉ ሲሆን የሕፃን እንክብካቤ በጠያቂው የሚገኝ ይሆናል።

### የሚቀጥለውን ወርክሾፕ ቦታና ቀጠሮ እንዴት መያዝ እችላለሁ?

ስለሚቀጥሉትአውደጥናቶችመረጃ ወይም ወርክሾፒ ስለሚካሄድበት ቦታ ቀጠሮ መያዣ በ email: financialworkshops@scottishrefugeecouncil.org.uk ወይም በድረገፃችን: http://www.scottishrefugeecouncil.org.uk/how_we_can_help/i_have_refugee_status/leave_to_remain_in_the_uk/financial_literacy_project


Scottish Refugee Council is a charity registered in Scotland.
Registered Charity: SC008639

የሚከተሉት መረጃዎች በአውደጥናቶች ውስጥ የተካተቱትን ርዕሶች ዝርዝር ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪ ገንዘብዎን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ይሰጣሉ።

**ባንኪንግ እና የቁጠባ ሂሳብ**

- **‘የባንክ ሂሣብ እንዴት መክፈት እንደሚቻል’** ብዙ የሆነ የባንክ ሂሣብ አይነቶች ያሉ ሲሆን እያንዳንዳቸው የተለያዩ አማራጮችን እና ባህሪያትን የተላበሱ ናቸው። ለተጨማሪ መረጃ የስኮትላንድን የስደተኛ ጉባኤ በራሪ ወረቀት ስለባንክ ሂሣብ አከፋፈት መመልከት ይችላሉ። : http://www.scottishrefugeecouncil.org.uk/assets/0000/0188/How_to_open_a_bank_account_June_2010.pdf
- ከባንክ ሂሣቦች ጋር አማራጭ የሆኑ ሂሣቦች **የብድር ማኅበራት** ሂሣቦች ናቸው። እነዚህ ከባንኮች ጋር ተመሳሳይ በሆነ አኳኋን የሚንቀሳቀሱ ሲሆን እጅግ አካባቢያዊ የሆኑ እና ከፋይናንስ ወይም ገንዘብ አገልግሎት በተጨማሪ የምክር አገልግሎትን ይለግሳሉ።
- **ይከታተሉ፡** እርስዎ የባንክ ወይም የብድር ማኅበራት ሂሣብ ከከፈቱ ወደ ሂሣብዎ የሚገባውን አግባብነት ያለውን ገንዘብ እና በአግባቡ ወጪ የሚደረገውን የገንዘብ መጠን መከታተል አስፈላጊ የሚሆነው እርስዎ ገንዘብ እንዳያጥርዎ አግባብነት የሌላቸው የባንክ የአገልግሎት ክፍያዎች እንዳይከፍሉ ለማድረግ ነው።

**መበደር**

- ገንዘብን ለመበደር የተለያዩ ቦታዎች እና ዘይቤዎች አሉ። እርስዎ ገንዘብን በተለያዩ ዘዴዎች ለመበደር የሚችሉት እንደ ብድር፣ በክሬዲት ካርዶች፣ በካታሎጎች፣ በየሳምንቱ ለመጋዘኖች የሚደረጉ ክፍየዎተ እና በኦቨርድራፍት ሊሆን ይችላሉ። እነዚህ ዘይቤዎች አልፎ አልፎ ለሸቀጥ ክፍያ የሚጠቅሙ ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ ለጥሬ ገንዘብ ግኝት የሚየገለግሉ ናቸው።
- ከላይ በተጠቀሱት ዘይቤዎች/መንገዶች ገንዘበን የመበደር የአገልግሎት ወጪ ይለያያል። ስለዚህ የብድሩን ደንቦች እና ግዴታዎች በአግባቡ/በደንብ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል።
- እርስዎ ገንዘብ ሲበደሩ ወለድ ታሳቢ ይደረጋል፣ ይህ ደግሞ በመባል የሚታወቀው APR በአመት የሚከፈለው መቶኛ (APR) ነው። በአጠቃላይ APR **መጠኑ ከፍተኛ ከሆነ እርስዎ በተመላሽ የሚከፍሉት የገንዘብ** መጠን ከፍተኛ ነው ማለት ነው።
- እርስዎ ደካማ የብድር ተመን ካለዎት ገንዘብ ለመበደር የሚቸግርዎ ይሆናል። የክሬት ተመን ማለት እርስዎ የተበደሩትን ገንዘብ ከባንክ ወይም ከሌላ አበዳሪ የወሰዱትን ብድር የመለሱበት የግምገማ ስልት ነው። የእርስዎ የብድር ተመን የሚወሰነው በብዙ ምክንያቶች ሲሆን የአድራሻዎ፣ የቅጥርዎ ሁኔታ፣ የገቢዎ እና የፍጆታ ክፍያዎን ታሪክ ከግምት ውስጥ የማያስገባ ነው።.
- እርስዎ ለብድር ለማመልከት መብት ይኖርዎታል። እርስዎ መስፈርቱን የማየሟሉ የብድር አይነቶች አንዳንዶቹ የሚያካትቷቸው፡ :
- **የUKBA በአንድ ቦታ የተሰበሰበ ብድር**

  የUKBA በአንድ የተሰበሰ ከብድር ብድር ነፃ የሚሆነው አዲስ ወደ ጽ/ቤቱ ለሚመጡ ስደተኞች ነው። ተጨማሪ መረጃን በሆም ኣፊስ ድህረ ገጽ : http://www.ukba.homeoffice.gov.uk/aboutus/workingwithus/workingwithasylum/integration/integrationloan/. ይመልከቱ።

  **የችግር ብድር**

-

  የችግር ብድር መጠን የሚሰጠው ለማኅበረሰብ ፈንድ በአደጋ ወይም በድንገተኛ ሁኔታ የአስቸኳይ የቤት ድጋፍ ለማድረግ ነው። ይህ ብድር ኋላ ላይ የሚከፈል ሲሆን በዚህ አይነቱ ብድር ምንም አይነት ወለድ አይታሰብም። ይህ ማለት ደግሞ እርስዎ የተበደሩትን የገንዘብ መጠን ብቻ የሚከፍሉ ይሆናል። ስለ ችግር ብድር የበለጠ መረጃ የብቁነት መስፈርቶተን ጨምሮ የማመልከቻ አደራረጉን ሂደት በድህረ ገጽ

  http://www.direct.gov.uk/en/MoneyTaxAndBenefits/BenefitsTaxCreditsAndOtherSupport/On_

a_low_income/DG_10018856 ይመልከቱ።

**የፍጆታ ክፍያ ደረሰኞች**

- እርስዎ የስደተኝነት ሁኔታ የተሰጥዎ ከሆነ ወይም በእንግሊዝ ንጉሳዊ መንግስት ውስጥ ለመቆየት ፍላጎት የሌለዎ ከሆነ እርስዎ የኤሌክትሪክ ኃይል እና የምግብ ማብሰያ ጋዝ ፍጆታዎችን ክፍያ ለመፈፀም ኃላፊነት ያለብዎ ሲሆን ለቤት መብራት እና ለማሞቂያ ለሚጠቀሙት የኃይል ፍጆታም ለመክፈል ኃላፊነት ይኖርብዎታል። እነዚህ የኃይል ፍጆታ ክፍያዎች እጅግ ውድ ሲሆኑ ዋጋዎቻቸው በአመቱ ውስጥ የሚለዋወጥ ነው። ስለዚህ እርስዎ እጅግ ከመጠን በላይ ላለመክፈል ወይም ከመጠን በታች ላለመክፈል እነዚህን ወጪዎች መቆጣጠር ይኖርብዎታል።
- እርስዎ የሚኖሩበት ቤት ቆጣሪ ሊኖረው ግድ የሚለው ሲሆን ወደቤቱ በገቡበት እለት ይህንን ቆጣሪ ወይም ቆጣሪዎች መውሰድ ይጠበቅብዎታል። ከዚያም ይህንን መረጃ በመጠቀም ለጋዝ/የኤሌክትሪክ አቅራቢ ኩባንያ ስልክ መደወል ይጠበቅብዎታል። በየጊዜው በመደበኛነት የኤሌክትሪክ የኃይል ፍጆታ ቆጣሪን ማንበብ እርስዎ ምን ያህል እንደተጠቀሙ ለማረጋገጥ የሚረዳዎ ሲሆን ይህ ደግሞ የፍጆታ ሂሣብዎን ለመገንዘብ ይረዳዎታል። ስለጋዝ እና የአሌክትሪክ ፍጆታዎች ተጨማሪ የምክር መረጃን ከስኮትላንድ የደንበኛ ድህረ ገጽ: http://www.consumerfocus.org.uk/scotland/files/2010/11/Tenants-advice-leaflet2.pdf ይመልከቱ።
- ለነዳጅ አጠቃቀምዎ በተለያዩ ዘዴዎች መክፈል የሚችሉ ሲሆን ለምሣሌ ያህል የፍጆታ መጠንዎን በፖስታ ቤት በኩል፣ በባንክ ወይም በቀጥታ ከባንክ ሂሣብዎ ተቀናሽ ተደርጎ እንዲከፈል ፍቃድ በመስጠት ሊሆን ይችላል። የፍጆታ ደረሰኞችን ክፍያዎች ማረጋገጥ እና በመኖሪያ ቤትዎ የተገጠመውን ቆጣሪ አንብቦ ማረጋገጡ እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህንን ካላደረጉ በቀላሉ የፍጆታ ክፍያ መጠራቀም ሊደርስብዎ ይችላል።
- ተጨማሪ የኃይል ፍጆታ ወጪዎችን ከስኮትላንድ የስደተኞች ምክር ቤት በራሪ ወረቀት ***በስኮትላንድ የሚኖሩ ስደተኞች የመኖሪያ ቤት፣ የኃይል ወጪዎች*** ከሚለው መመሪያ እና በድህረ ገፃችን http://www.scottishrefugeecouncil.org.uk/assets/0000/0215/L8_-_fuel_poverty18__Nov_2009.pdf መመልከት ይችላሉ።

**ኢንሹራንስ/መድህን**

- የተለያዩ የኢንሹራንስ ሽፋኖች ያሉ ሲሆን ለምሣሌ የሕይወት ኢንሹራንስ፣ የግለሰብ የጤና ኢንሹራንስ፣ የቤት ቁሳቁሶች ኢንሹራንስ፣ የክፍያ መጠበቂያ ኢንሹራንስ እና የተሽከርካሪ ኢንሹራንስ ናቸው።
- መኪና የሚያሽከረክሩ ከሆነ ቢያንስ የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ሊኖርዎ ይገባል የሚል ቢሆንም ሌሎቹ የኢንሹራንስ አይነቶች አማራጭ ናቸው።
- አንዳንድ ጊዜ የቤት ባለቤቱ የቤት ይዘቶችን ኢንሹራንስ በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ወይም እንዲገዙ ሁኔታዎችን ሊያመቻችልዎ ይችላል። በሕይወትዎ በተለያዩ ጊዜያት ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሚሉትን የኢንሹራንስ አይነቶች ሊመርጡ ወይም ከግንዛቤ ሊያስገቡ ይችላሉ።
- እርስዎ ኢንሹራንስ በቀጥታ ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች በስልክ ወይም በድህረ ገጽ በመገናኘት ለመግዛት ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ ኢንሹራንስን ከባንኮች፣ ከታላላቅ የገበያ አዳራሾች እና ከሌሎች ሱቆች መግዛት ይችላሉ። እርስዎ የላቀ ዋጋ ወይም ተወዳዳሪ የሆነ ዋጋን ለማግኘት በአካባቢዎ የሚገኙ ሱቆችን ዋጋዎች ማወዳደር የሚችሉት ከድህረ ገጽ http://www.gocompare.com/ በመጠቀም ይሆናል።

**ወደ ስራ መግባት**

- እርስዎ እዚያ መስራት ሲጀምሩ በሚያገኙት ጥቅሞች ላይ ለውጦች ሊደረጉ ይችላሉ። የሥራ ማዕከሉ እና ሌሎች በአካባቢዎ የሚገኙ በገንዘብ ላይ ምክር የሚለግሱ ኤጀንሲዎች ለእርስዎ 'በተሻለ የሥራ ስሌቶችን ሊሰሩልዎ የሚችሉ'ሲሆን ይህም እርስዎ በገንዘብ ረገድ የተሻለ ስራን ለመምረጥ የሚችሉ ውሣኔዎችን እንዲወስኑ ይረዳዎታል። ከዚህም በተጨማሪ ምን አይነት ጥቅሞች ለመውሰድ መብት እንዳለዎ ያብራራሉ። ሙሉ ጊዜን በትምህርት ለማሳለፍ መሞከር ወይም መወሰን ጥቅሞችዎ ላይ ተፅእኖ ያደርሳል። በጥቅሞች ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ Directgov ድህረገጽን http://www.direct.gov.uk/en/Diol1/DoItOnline/DoItOnlineByCategory/DG_172666 ይመልከቱ።
- እርስዎ መስራት ሲጀምሩ መደበኛ የክፍያ ደረሰኝ የሚሰጥዎ ሲሆን ምን ያህል እንዳገኙ እና ከጠቅላላ ክፍያዎ ላይ ተቀናሽ የተደረገውን የገንዘብ መጠን ያሳይዎታል። እርስዎ ሁሌም የገቢ ግብር እና የብሔራዊ ኢንሹራንስ ክፍያን ይከፍላሉ፤ በትክክል የሚከፍሉት የገንዘብ መጠን የሚመረኮዘው በብዙ ምክንያቶች ላይ ሲሆን እርስዎ በዓመት ገቢዬ ነው ብለው የሚጠብቁትን የገንዘብ መጠን ጨምሮ ወይም እርስዎ ከአንድ ሥራ በላይ ያለዎት ከሆነ ነው።
  ስለ ተቀናሾች እና ገንዘብዎን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ የቢቢሲ ቪዲዮ ድህረገጽ http://www.bbc.co.uk/raw/money/new_job/managing_while_you_work.shtml ይመልከቱ።

**የራስዎን የግል ሥራ መጀመር**

- እርስዎ የራስዎን የግል ሥራ ለመጀመር ከፈለጉ ወይም የራስዎ ቀጣሪ መሆን ከፈለጉ በነፃ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ብዙ ድርጅቶች ይገኛሉ።
  - “Business Gateway” የመነሻ ምክር እና መረጃ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ለነባር የንግድ ተቋማትም ይሰጣል።
    ለተጨማሪ መረጃ የድርጅቶቹን ድህረ ገጽ በ: http://www.bgateway.com ይመልከቱ።
  - HMRC (የንግስቷ የገቢ እና ጉምሩክ) የግብር ተመላሾችን ለማሰላት ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው። ለተጨማሪ መረጃ የHMRC ድረገጽ : www.hmrc.gov.uk ይመልከቱ።

**ተጨማሪ የገንዘብ ምክርን ከየት ማግኘት እችላለሁ?**
በእነዚህ ኮርሶች ወይም ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ መረጃን የሚፈለጉ ከሆነ የስኮትላንድ የስደተኞች ምክር ቤትን አባል በሚከተለው አድራሻ ያግኙ: Financialworkshops@scottishrefugeecouncil.org.uk ወይም በስልክ ቁጥር 0141 248 9799.

ከግላስጎው ምክር እና የመረጃ ኔትወርክ ነፃ፣ ሚስጥራዊ እና ገለልተኛ ምክር ያግኙ። የግላስጎው (GAIN) (የግላስጎው የምክር እና የመረጃ ኔትወርክ) በድረገጽ www.gain4u.org.uk ስለ ኤጀንሲው ዝርዝር መረጃ በአቅራቢያዎ ያለውን አጀንሲ ይጠይቁ ወይም በስልክ ቁጥር 0808 801 1011 ደውለው ይጠይቁ።